AEPAC

American Ethiopian Public Affairs Committee

## ጋዜጣዊ መግለጫ

## በኢትዮጵያ ህገ መንግሥት መሻሻል ምክክር ለማድረግ ለዳያስፖራው ኮሙኒቲ ጥሪ

የአሜሪካ ኢትዮጵያዊያን የሕዝብ ጉዳዮች ኮሚቴ-ኤፓክ (The American-Ethiopian Public Affairs Committee-AEPAC)፤ አንድ ሚልዮን ገደማ ይጠጋል ተብሎ የሚገመተዉና፤ በአሜሪካ የሚኖረዉ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ፤ በእናት ሀገሩ ኢትዮጵያ ሊካሄድ በታቀደው "ብሄራዊ ምክክር" የመካፈል ዕድል እንዲያገኝ በሚል አዲስ መድረክ ከፍቷል፤ የእዚህ መድረክ ዋና ትኩረት የኢትዮጵያን እና ትዉልዶቿን መጭ ዕድል ወሳኝ በሆነውና አንገብጋቢው ጥያቄ "በህገመንግሥቱ መሻሻል" ላይ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ፤ ባለፉት አሰርት አመታት ያላየችው አይነት ከባድ ፈተናና መከራ የለም ማለት ይቻላል፡፡ በዘር፤ በቋንቋ፤ በሀይማኖት፤ በመሬት፤ በክልልና በጎጥ ባለቤትነት ጥያቄና ልዩነት ላይ ያተኮሩ መከፋፈሎችና ግጭቶች የተነሳ፤ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ዜጎቿን አጥታለች፡፡ ከመሬታቸው፤ ቤታቸውና ንብረታቸው እየተፈናቀሉ ወደ በረሀና ዱር የተሰደዱ፤ ከእነቤተሰቦቻቸው ለአዉሬ የተጋለጡ መአት ናቸው፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው አንዱም፤ ለስልጣን ሽሚያ በሚያፈነግጡ የፖለቲካ መሪወችና "የብሄር ነጻ አዉጭ" ነን በሚሉ የታጠቁ ድርጅቶች በሚቀሰቀሱ ጦርነቶች ሳቢያ ነው፡፡ በእነዚህ ጦርነቶች ብቻ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሀን ዜጎች በግፍ ተጨፍጭፈዋል፡፡ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ፤ በድህነት፤ በበሽታ፤ በድርቅና በእረሀብ ላይ፤ ይህ ሁሉ መከራ ተደራርቦባቸው፤ በሚልዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዉያን "መቸ ይሆን የሚያልፍልንና ቀን የሚወጣልን" እያሉ ዘወትር እራሳቸዉን በመጠየቅ፤ ለፈጣሪያቸዉ ሌትና ቀን እንደጸለዩ በተስፋና በእሮሮ ሲኖሩ አመታትን አሳልፈዋል፡፡

ምናልባትም ሀገራችን እነዚህን ሁሉ ከባድ ፈተናወች እንድታልፍ፤ እልቂቱንና መከራዉን አስቁሞ፤ ሰላምና የፖለቲካ መረጋጋት ለማስፈን ቢአግዝ፤ ብሎም ድህነትን ለማጥፋትና ኤኮኖሚዉን ለማሳደግ ቢረዳ በሚል፤ በስልጣን ላይ ያለው መንግሥት ከታህሳስ 20 ቀን 2014 ዓ.ም (December 29, 2021) ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ አዲስ አዋጅ አዉጥቷል፡፡ "የብሄራዊ ምክክር" በሚል በሀገር አቀፍ ደረጃ ዉይይት እንዲካሄድ ወስኖአል፡፡ በሀገሪቱ ሰላምንና መረጋጋትን፤ ብሄራዊ ስሜትንና አንድነትን ያመጣል በሚል "የብሄራዊ ምክክሩ" ትልቅ ተስፋ ተጥሎበታል፡፡

ይህን "ብሄራዊ ምክክር" የሚያቀናብርና የሚመራም "የብሄራዊ ምክክር ኮሚሽን" የተባለ ኮሚቴ በአዋጁ ተቋቁሟል፤ የእዚህ ኮሚሽን ኃላፊነትና ተግባር፤ በሀገር አቀፍ ደረጃና በህብረተሰቡ መሀል ተሰሚነት ያላቸዉንና ተጽእኖ አሳዳሪ የሚባሉትን ዜጎች ለምሳሌ የፖለቲካና ሀይማኖት መሪወችን፤ እንዲሁም ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ለምሳሌ ወጣቶችን፤ ሴቶችን፤ ምሁራንንና ዳያስፖራዉን የሚያሳትፍ መድረክ ማመቻቸትን ያካትታል፤ ከእዚህ ጋር በማያያዝ ኮሚሽኑ፤ በልዩ ልዩ መድረኮች ሕዝቡን በንቃትና በነጻ ያለሰቀቀን እንዲሳተፍ ማበረታታት ይጠበቅበታል፡፡

በሀገሪቱ አሉ በሚባሉ አንገብጋቢ ችግሮችና መፍትሄወቻቸው ላይ ሕዝቡ እንዲወያይ በማድረግ፤ ከተለያዩ አቅጣጫወች የሚቀርቡትን ሀሳቦችና አስተያየቶች ጨምቆ፤ ዋና ዋናወቹን በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚካሄደው "ብሄራዊ ምክክር" ማቅረብና ዉይየቱን የመምራት ኃላፊነትም ለእዚህ ኮሚሽን ተሰጥቶታል፤ በመጨረሻም ኮሚሽኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ በብሄራዊ ምክክሩ ቀርበውና ተብላልተው፤ በሕዝቡ የተደረሰባቸዉን ዋና ዋና ችግሮች ከእነመፍትሄወቻቸው መርምሮና አገናዝቦ፤ የእራሱን አስተያየት በመጨመር፤ ዉሳኔ እንዲደረግባቸው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

ኤፓክ፤ ዋናዉና በአንደኛ ደርጃ ሊጠቀስ የሚገባዉ የኢትዮጵያ ችግር፤ አሁን በሀገሪቱ ያለው ህገ መንግሥት ነው ብሎ ያምናል፤ ይህ ህገመንግሥት ለችግሮች መፍትሄ ከመስጠት ይልቅ ችግር ፈጣሪ፤ ከሕዝብ አንድነት ይልቅ ከፋፋይ፤ ከሰላም ይልቅ እርስበርስ መጋጨትን የሚያበረታታና፤ ፍጹም ኋላቀር ነው ብሎ ያምናል፤ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ አንስቶ፤ ላለፉት ሰላሳ ዓመታት ያክል፤ ሀገራችን በጣም ብዙ ዉስብስብ የፖለቲካ፤ ህብረተሰብና ኤኮኖሚ ችግሮችና ፈተናወች አጋጥመዋታል፤ እነዚህም ፈተናወችና ችግሮች አብዛኞቹ ምንጫቸው ከህገመንግሥቱ ጋር የተያያዘ ነው ማለት ይቻላል፤ ስለዚህ አሁን ያለዉን ህገመንግሥት ማሻሻሉ አማራጭ የሌለዉና በብሄራዊ ምክክሩ ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ነው ብሎ ኤፓክ ያምናል፡፡

ባለፉት አሰርት አመታት ህገመንግሥቱ በሀገሪቱ ነጻነትን፤ ፍትህንና እኩልነትን ማዳበሩ ቀርቶ፤ ግፍን፤ መከራን፤ አፈናን፤ የተፈጥሮ፤ የሰብአዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች እረገጣንና ሙስናን ነው እየኮተኮተ ያሳደገው፤ በፈለጉበት ቦታ የመኖርና በነጻ የመንቀሳቀስን መብት ገፍፎ፤ በምትኩ ዜጎችን በቋንቋ፤ ዘር፤ ብሄርና ክልል አጥሮና ከፋፍሎ፤ ለማያባራ የእርስበርስ ግጭት እየዳረገ ሰላም በማሳጣት፤ ሀገራችንን ለጥፋት ዉሀ ነው የዳረጋት፡፡ የዴሞክራሲ መሠረታዊ ስነ ሀሳብ የሆነው፤ የመንግሥት ስልጣን ክፍፍልና ቁጥጥር እንዳይኖር በማድረግ፤ በየእርከኑ ባሉት መዋቅሮች የግለሰለቦች አምባገነንነትን እያዳበረ፤ ምስኪኑን ሕዝብ ሲያስረግጥ፤ ሲያስመርር፤ ሲያሰቃይና ሲያስጠፋ ነው አመታትን ያሳለፈው ቢባል ማጋነን አይሆንም፡፡ የመንግሥት ባለሥልጣኖች፤ ከፖሊስና ፍርድ ቤቶች ጀምሮ እስከ ክልልና የበላይ መሪወች ድረስ በነጻ የመናገርና የመጻፍ መብትን እየገፈፉ፤ ጋዜጠኞችንና ፖለቲከኞችን፤ ወጣቶችንም እንደፈለጉ ያለፍርድ የሚያሳስሩበት፤ የሚያሰቃዩበት፤ በግፍ የሚያስፈርዱበትና፤ ከሀገር የሚያሰድዱበት ፍትሕ የለሽ ሥርአት በሀገሪቱ እንዲሰፍን ነው ህገመንግሥቱ ያመቻቸው ማለት ይቻላል፡፡

*******

ባለፉት ሁለት አመታት፤ በሰሜን ኢትዮጵያ በተቀሰቀሰው ጦርነት ሳቢያ፤ ሀገራችን በዉስጥና የዉጭ ጠላቶች ተወጥራ ከባድ ፈተና ወስጥ በገባችበት ወቅት፤ የዳያስፖራዉ ኮሙኒቲ ከጫፍ እስከጫፍ በከፍተኛ የሀገር ፍቅር ስሜት ተቀስቅሶ በመነሳትና በአንድነት በመቆም፤ ሀገሩን ለማዳን ብዙ ተረባርቦአል፤ በዚህ ትግሉም፤ በርካታ ስኬቶችን አስገኝቷል፡፡ ይህ ዛሬ ለተገኘው ጊዜአዊ ሰላምም፤ የዳያስፖራዉ አስተዋጽኦ በቀላሉ የሚገመት አይደለም፡፡ በእዚህ የትንቅንቅ ትግል ወቅት፤ ምንም እንኳን ከተቋቋመ ገና ብዙ ዓመት ያላደረገና ታዳጊ ድርጅት ቢሆንም፤ ኤፓክ አኩሪ የሚባሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦወችን አበርክቷል፤ ዳያስፖራዉን በማንቃት፤ በማደራጀትና በመቀስቀስ፤ ብሎም በኢትዮጵያ ሀገራችን ላይ እየተሰራ ያለዉን ግፍ በማጋለጥና፤ ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ኃያላን ጠላቶች ጋር በተለያዩ መድረኮች ፊትለፊት በመጋፈጥ፤ በርካታ ድሎችን በማስገኘት ሀገራዊ ግዴታዉን ተወጥቷል፡፡

ኤፓክ፤ ይህ አሁን የከፈተዉ አዲስ የምክክር መድረክም፤ ሀገራችን በጦርነቱ ወቅት ባሳላፈቻቸዉ የፈተና አመታት ዳያስፖራዉ ባስገኛቸው ስኬቶችና ባዋጣዉ ድርሻ ላይ በመቀጠል፤ የሰላማዊ ትግሉን እንዲያሳድግና፤ የሀገራችንን መጭ ዕድል በመወሰኑም ላይ አንደሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳታፊ እንዲሆን፤ ብሎም ድምጹን እንዲያጋራ፤ ሁኔታወችን ለማመቻቸት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፤ በተለይም አሁን ያለው የኢትዮጵያ ህገ መንግሥት ባስከተለው መዘዝና፤ እንዴትስ ሊሻሻል ይችላል በሚለው ምክክር ላይ፤ ለዳያስፖራዉ ሀሳቡን እንዲሰጥ ዕድል ያስገኛል በሚል ዓላማ ነው፡፡ ዋና ዋናወቹ የሀገራችን ችግሮች ከህገ መንግሥቱ፤ የአገዛዝና የክልል ወይም “ፌደራል መዋቅሩ” ጋር እንደሚያያዙ እምነታችን ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች እያነጠሩ በማዉጣት፤ በስሜት ሳይሆን በጥናትና በእዉቀት ላይ በተመሰረቱ ተጨባጭ ማመሳከሪያወች በመመርኮዝ፤ ሁሉም የዳያስፖራ አባላት በመድረኩ በመሳተፍ ሀሳባቸዉን እንዲሰጡ ኤፓክ ከልብ ያበረታታል፤ አሁን በሀገራችን ያለው ህገመንግሥት፤ መሠረታዊ የሆኑትን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለማስከበር፤ ለልማትና እድገት አመች ሁኔታወችን ለመፍጠርና፤ ሰላምና መረጋጋትን መቻቻልን ለማጠናከር የሚችልባቸዉን ዘዴወች ለማካተት፤ እንዴት ቢሻሻል ይሻላል በሚሉት ሀሳቦች ዳያስፖራዉ ተወያይቶ ለብሄራዊ ምክክሩ አስተያየቱን እንዲያቀርብ ኤፓክ ሁኔታወችን በሚገባ ያመቻቻል፤ ያቀናብራል፤ ግንባር ቀደም ሆኖም ያስተባብራል፡፡

*******

**የኤፓክ ሊቀ መንበር መስፍን ተገኑ እንዳለው፡**

“የኤፓክ የዉይይት መድረክ፤ በሀገራችን በሚካሄደው በዚህ ታሪካዊና ብሄራዊ እንቅስቃሴ፤ ዳያስፖራዉ ዋናው የሀገሩ ችግር፤ ህገመንግሥቱ እንዴት ይሻሻል በሚለው ሀሳብ ላይ ድምጽ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ ስር ከሰደደው ኋላ ቀር የዘረኝነት ስርአት ሀገራችን ነጻ ወጥታ፤ ነጻነት፤ ፍትህና እኩልነት በሰፈነበት፤ ዘመናዊና፤ የህብረ ብሄራዊ አንድነት ጎዳና እንድትጓዝ የሁላችንም ምኞት ነው”

“ኢትዮጵያ በዘር፤ ቋንቋና ክልል ላይ በቆመ ከፋፋይ መዋቅር ሳይሆን፤ በእዉነተኛ የፌደራል ስርአት መተዳደር አለባት፤ የዜጎቿ ማንነት፤ በዘራቸውና ብሄራቸው ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው ብቻ ተለይቶ መታወቅ ይኖርበታል፤ የቋንቋና ብሄር ልዩነታችን ክብራችን፤ የግሩም ታሪካችን፤ መልካም ባህላችንና የህብራችን ዉበት መለያ እንጅ፤ የእርስበርሳችን መናቆሪያና መከፋፈያ፤ መጋጫ መሆን የለበትም”፡፡

ይህ “የኤፓክ ድያስፖራ ምክክር” ወይም ዉይይት መድረክም፤ በኤፓክ ሊቀመንበር መስፍን ተገኑና፤ በታዋቂው ኢትዮጵያ አሜሪካዊ የህግ ባለሞያ፤ በደረጀ ደምሴ ተባባሪነት ይመራል፤ ለእዚህ ፕሮጀክት አማካሪና አደራጅ ኮሚቴም በቅርቡ ኤፓክ ያቋቁማል፡፡ በሚመጡት ወራት ይህ ኮሚቴ ከዳያስፖራዉ ኮሙኒቲ ሀሳቦችንና አስተያየቶችን ይሰበስባል፤ ዉይይቶችንም እያቀናጀ ይመራል፤ የተለያዩ ምርምሮችንና ጥናቶችን በማሳተምና በሚድያ በማዉጣት ለኤፓክ አባላትና ለዲያስፖራው ኮሙኒቲም ያሰራጫል፤ በተከታታይና በመጨረሻም የእነዚህን ሀሳቦችና ጥናቶች ዋና ዋና ነጥቦች እየጨመቀ አጠናቅሮ፤ በአስተያየት መልክ ለብሄራዊ ምክክሩ ኮሚሽን ያቀርባል፡፡
ይህ ታሪካዊ ዕድል እንዳያልፋችሁ! በእናት ሀገራችሁ በኢትዮጵያ ህገ መንግሥት መሻሻል አሻራችሁን ለማስቀመጥ በንቃት እንድትሳተፉ በትህትና እናሳስባለን!

ለዉይይት መድረኩ አማካሪ ኮሚቴ አባላት ስም ለመጠቆምና ለተጨማሪ መረጃም ወደ
https://ethiopianconstitutionreform.com አምርታችሁ ብይነ መረባችንን እንድትጎበኙ በትህትና እንጋብዛለን፤

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር!
መልካም አዲስ አመት!
ለሀገራችን ዘላቂ ሰላም ያዉርድልን!

መስፍን ተገኑ
የኤፓክ ሊቀ መንበር
ጥር 5 ቀን 2015 ዓ.ም (January 13, 2023)